## ነፃነት፣ ሉኣላዊነትና ዴሞክራሲ ኣሁንም ያሸንፋሉ!

### ከኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ኣስተባባሪ ጉባኤ (ኦህኣኣጉ)

### እና

### ከብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ)

### የቀረበ የጋራ ጥሪ

በኦሮምያ የሚቀጣጠለው ኣብዮት ባለፉት ኣስር ኣመታት ሲካሄድ የቆየው የፀረ ጭቆና ኣመጽ (FDG) ቀጣይ ኣካል ነው። ይህ ኣብዮት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የተጫነው የእስራት፣ የግድያ፣ የኣፈና፣ የዘረፋ፣ ከቀዬው ላይ የማፈናቀልና ባጠቃላይ ከመቶ ኣመታት በላይ የኦሮሞ ህዝብ የተፈራረቀበት ግፍና በደል እንዲያበቃ የሚያስገድድ ታላቅ ኣብዮት ነው። ላለፉት መቶ ሰላሳ ኣመታት የኦሮሞ ህዝብ የተዳረገበት ውርደት ማብቂያ እንዲበጅለት ለማስቻል የሚካሄድ ፍትሃዊ ኣብዮት በመሆኑ ስኬትና ድል የሚገባው ኣብዮት ነው። በገፍ ሲፈስ የኖረው የኦሮሞ ልጆች ደም እንዲያቆም፣ በብሶት ሲንቆረቆር የኖረው የህዝቡ እንባ ኣንዲደርቅ፣ በኦሮምያ የሚፈፀመው ጭፍን የዘረፋ ተግባር ኣክትሞ ኦሮሞ የሃብቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል በሰላማዊ መንገድ የሚካሄድ ኣብዮት ነው።

በቱኒዝያ፣ በግብፅና በመካከለ ው ምስራቅ ሃገሮች የተካሄዱና እየተካሄዱ ያሉት ኣብዮቶች የኦሮሞ ወጣቶች ከተያያዙት የፀረ ጭቆና ኣመፅ በሁዋላ የተቀጣጠሉ ኣብዮቶች ናቸው። የፀረ ጭቆና ኣመፁና የቄሮው ንቅናቄ እንዲሁም መላው ህዝባችን ለመብቱ መከበር የሚያደረገው ትግል የኣረቡ ኣለም ኣብዮት ኣይነት ድል የሚገባው ነው። ያለንበት ኣጠቃላይ ሁኔታ ዴሞክራሲና የህዝቦች ድምፅ በኣምባገነን ስርኣቶች ላይ ድል መቀዳጀቱ ኣይቀሬ መሆኑን ያስመሰከረ ነው። ስለሆነም ባለፉት መቶ ሰላሳ ኣመታት በኦሮሞ ህዝብ ላይ የደረሰው እስራት፣ ግድያ፣ ኣፈና፣ ዘረፋ፣ ከኣያት ቅድመ ኣያት ቀዬ መፈናቀልና ባጠቃላይ የጭቆና ኣገዛዙ

እንዲያበቃ ለማድረግ የታቀደውን ይህን ታላቅ ኣብዮት ለማሳካት የኦሮሞ ህዝብ በነቂስ እንዲወጣና በተለይም ወጣቱ ትውልድ እንደተለመደው የፋና ወጊነቱን ሚና በብቃት እንዲጫወት የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ኣስተባባሪ ጉባኤ (ኦህኣኣጉ) እና ብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ) በጋራ በመሆን ጥሪ ያቀርባሉ።

ከተለያዩ የህብረተሰባችን ክፍሎች የተውጣጣን የኦሮሞ ልጆች የተረገጠውን መብታችንን ለማስመለስ በሰላማዊ መንገድ ኣብዮት ለማካሄድ መዘጋጀታችንን እንደ ው ሁሉ በጭቆና ቀንበር ስር ለሚማቅቁ ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦችና ለመላው የኣለም ማህበረሰብ ስናሳውቅ ኣብዮቱ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ በመሆን ጭምር ነው። በእስካሁኑ የህዝባችን የነፃነትና የዴሞክራሲ ትግል ለተከፈሉ መስዋእትነቶች ክብር ከፍተ ቦታ እየሰጠን እ ም በተራችን ለነፃነት፣ ለሉኣላዊነትና ለዴሞክራሲ በቀደምት ታጋዮቻችን የተከፈሉትን ውድ መስዋእትነቶች ፍሬያማ ለማድረግ እነሆ ቆርጠን ተነስተናል። ስለሆነም እንደ ኦሮሞ ህዝብ ሁሉ የጭቆናው ስርኣት ገፈት ቀማሽ የሆኑት የተቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦችም ጥሪያችንን ሰምተው በሁላችንም ላይ የተጫነውን የጭቆና ቀንበር በጋራ ኣሽቀንጥረን ጥለን በምትኩ ነፃነት፣ ሉኣላዊነትና ዴሞክራሲ ሰፍነው በሃገራችን ላይ በሰላምና በብልፅግና እንኖር ዘንድ በቁርጠ ነት ከጎናችን እንዲሰለፉ ወቅታዊ ጥሪ እናስተላልፋለን።

**ኣብዮቱን ለማቀጣጠል ካስገደዱን ኣበይት ነጥቦች በጥቂቱ፣**

1. በኢንቬስትመንት ስም በኦሮምያ ገጠሮችና ከተሞች በተለይም ደግሞ በፍንፍኔ ዙሪያ ህዝባችንን ከቀዬው ማፈናቀል፣ የኦሮምያን የተፈጥሮ ሃብቶች (በተለይም እንደ ወርቅ ያሉ ውድ ማእድናትን) መዝረፍና ማውደም ባለፉት ሃያ ኣመታት ኣሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለደረሰ
2. የመላው ኦሮምያ ህዝባችን በተለይም ደግሞ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና በሁለተ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የኦሮሞ ተማሪዎች ባለፉት 20 ኣመታት ሲያነሷቸው ለኖሩት ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሽ እስራት፣ ግድያ፣ ኣፈናና ወከባ ብቻ ስለሆነ
3. በተለይም በቅርቡ የፍንፍኔ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎችና በፍንፍኔ ዙሪያ የሚገ - የገላን ጉዱ፣ የቃሊቲና የዋጂቱ ኣካባቢ ኣርሶ ኣደሮች እንዲሁም የኣዳማ ዩኒቨርሲቲ፣ የወለጋ ዩኒቨርሲቲና የሃረማያ ዩኒቨርሲቲ የኦሮሞ ተማሪዎች ያቀረቧቸው የመብት ጥያቄዎች ፍትሃዊና መላው የኦሮሞ ህዝብ ሊደግፋቸው የሚገባ ጥያቄዎች መሆናቸውን ስለተረዳን
4. የኦሮሞ ህዝብ ከማን ውም ጊዜ በላይ ባለፉት 20 ኣመታት በገፍ ለእስራት እየተዳረገ መሆኑን ከግምት በማስገባት ይህ የእስራት እርምጃ ባስቸኩዋይ እንዲቆምና ላለው የፖለቲካ ችግር መንግስት በሰላማዊ መንገድ የኦሮሞና የሌሎችም ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጥያቄ እንዲመልስ እንዲሁም በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያወጀውን የሽብር ዘመቻ ለማስገታት መታገል የግድ በመሆኑ
5. ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች የሚመረቁ ተማሪዎች ስልጣን ላይ ያለው መንግስት በሚከተለው ኣድሎኣዊ ፖሊሲ ሳቢያ ለስራ ኣጥነት ተዳርገው ስራም ለመፍጠር እድል ስላልተመቻቸላቸው መፃኢ ህይወታቸው በመጨለሙ
6. መሬትን በሊዝ ስሪት ለማስተዳደር በቅርቡ የተነገረው ኣዋጅ ህዝብን ያላማከረና ክፉና ደጉን ያላገናዘበ ከመሆኑም በተጨማሪ ህዝቦች በመሬታቸውና በተፈጥሮ ሃብታቸው ላይ ያላቸውን ህጋዊ የባለቤትነት መብት የሚያፍን በመሆኑ
7. ባሁኑ ጊዜ "ቅድሚያ ለኣባይ ግድብ" ስለተባለ ሌላ ኣይነት ልማት ማካሄድ ከሽብርተ ነት ተለይቶ ስለማይታይ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ "ቦንድ ግ ـ" እና የኣባይ

ግድብ ግንባታ መዋጮ እየተባለ የህዝቡን አቅም ያላገናዘበ የገንዘብ መዋጮ በህዝብ ላይ መወሰኑ አይን ያወጣ ዘረፋ በመሆኑ

8. ስልጣን ላይ ባሉት ጥቂት ግለሰቦች በሞኖፖል የተያዘው የገበያ ስርኣት ፍትሃዊ ባለመሆኑ ባሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነት ተባብሶ እጅግ የመረረ ደረጃ ላይ መድረሱ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑ በመረጋገጡ
9. የኦሮሞ ህዝብ የትግል መሰረት የሆነው የመጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር ቢሮ መዘጋቱ፣ አመራሩ መታሰራቸውና የማህበሩ እንቅስቃሴ መታገዱ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ከተከፈቱት የጥቃት ዘመቻዎች መካከል አንዱ በመሆኑ
10. ብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ) በሰላማዊ መንገድ ባነሳው የኦሮሞ ህዝብ የመብት ጥያቄ የተገ  ምላሽ እስራት፣ ግድያ፣ ወከባ፣ ከትምህርት ገበታ መባረርና ለስደት መዳረግ ብቻ ስለሆነ
11. "ለፕሮጀክቶች የተመደበ ገንዘብ ስለተመዘበረ ሙስናን እናስወግድ" እየተባለ ባሁኑ ወቅት በኦሮምያ ሁሉም የልማት ፕሮጀክቶች እንቅስቃሴያቸው እንዲቋዋረጥ ተደርጎኣል። የኦሮምያ የመንግስት ሰራተኞች ባሁኑ ጊዜ በሲቪል ሰርቪስ ካድሬያዊ ስልጠናና "ሽብርተ ነትና ሙስናን እናስወግድ" በሚል ያልተቋዋረጠ ስብሰባ በመጠመዳቸው ከኣስተዳደራዊ የልማት ስራ እንዲርቁ ተደርገዋል። የፌደራሉ መንግስት በኦፒዲኦ ኣባሎች ላይ ኣመኔታ በማጣቱ በኦሮምያ ክልል የኣስተዳደር ሃላፊነት በመለስ ዜናዊ የደህንነት መዋቅር ስር እንዲገባ ተደርጎኣል። ይህ ኣዝማሚያ ቀስ በቀስ የኦሮምያን ክልላዊ መንግስት ኣስተዳደር ኣፍርሶ በኣንድ ግለሰብ በሚመራ ፈላጭ ቆራጭ ኣምባገነናዊ ስርኣት ስር ለማስገባት ያለመ ስለመሆኑ ፍንጮች ስለሚታዩ
12. ባጠቃላይ እስራት፣ ግድያ፣ ከስራ መባረር፣ ከገዛ ቀዬ መፈናቀል፣ ከትምህርት ገበታ መባረርና ሌሎችም ላለፉት 20 ኣመታት በኦሮምያ እየተወሰዱ ያሉ በጭካኔ የተሞሉ እርምጃዎች ባስቸኩዋይ ማብቃት ኣለባቸው።

**ስለሆነም**

1. ስርኣቱ የሃገሪቷን ህዝቦች ፍትሃዊ ጥያቄዎች ለማፈን ሲል በኦሮምያና በሌሎችም ክልሎች ባለፉት 20 ኣመታት ሲያካሄድ የቆየውን ወታደራዊ ዘመቻ እንዲያቆምና ለራስን እድል በራስ የመወሰን ጥያቄ ትክክለ  ምላሽ እንዲሰጥ እንጠይቃለን።
2. የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኩዋይ እንዲፈቱ፣ የሰው ልጅ ኢሰብኣዊ በሆነ ሁኔታ ሰቆቃ የሚፈፀምበት፣ በድብደባ ኣካሉ የሚጎድልበትና እንደ ከብት የሚታረድበት፣ በዚህም እስካሁን የሺዎች ህይወት በኣስቃቂ ሁኔታ የጠፋበት *ማእከላዊ የወንጀል ምርመራ* የሚባለው እስር ቤት ባስቸኩዋይ ይዘጋ እንላለን።
3. በሁሉም የሃገሪቷ ህዝቦች በተለይም ደግሞ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ባለፉት 20 ኣመታት ስር የሰደደው የእስራት፣ የግድያ፣ የኣፈና፣ ከስራ የማፈናቀልና የወከባ ዘመቻ ኣሁኑኑ እንዲያበቃ እንጠይቃለን።
4. ህዝቦችን ለኣሳሳቢ ድህነት ያጋለጠውና ጥቂቶች ብቻ እንዳሻቸው የሚከብሩበት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ባስቸኩዋይ እንዲስተካከልና ውሎ ሳያድር በመንግስት ኣመራር ኣካላት በሞኖፖል የተያዙ የንግድ ተቋዋማት እንዲፈርሱ።
5. በኢንቬስትመንት ስም የሃገሪቷን ህዝቦች በተለይም ደግሞ የኦሮሞን ህዝብ በገፍ ከቀዬው ማፈናቀል እንዲቆም፣ እንደወርቅ ያሉ እጅግ የከበሩ የኦሮምያ ማእድናት ዘረፋ ባለበት እንዲገታ፣ ከውጭ ከመጡ ባለሃብቶች ጋር የተቀናጀ በህዝብ መሬትና ሃብት ላይ ያነጣጠረው የመሬት ኪራይና ሽያጭ ስምምነት ባስቸኩዋይ እንዲፈርስ እንጠይቃለን።

6. ኢትዮጵያ ባለፉት 20 አመታት በፖለቲካው፣ በማህበራዊውና በኢኮኖሚው መስክ ለባሰ ቀውስ የተዳረገች ሲሆን ለዚህም ተጠያቂ የሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከስልጣን ወርደው ቢሮአቸውን እንዲለቁ እንፈልጋለን።
7. ባለፉት አመታት በሃገሪቷ ተካህደዋል የሚባሉት ምርጫዎች አሳፋሪ ከመሆናቸውም ባሻገር የምርጫ ድራማዎቹ አላማ የአለምን ማህበረሰብ ለማታለል የታሰበ ርካሽ የፖለቲካ ጨዋታ መሆኑ በግልፅ ስለሚታወቅ ሁለቱ የሃገሪቷ ምክር ቤቶች ባስቸኩዋይ ይፍረሱ እንላለን።
8. ፍትህና ዴሞክራሲን በሃገርቷ ለማስፈን ከተፈለገ ለህዝቦች ነፃነትና ዴሞክራሲ መረጋገጥ በሃቅ የሚታገሉትንና ለሰብአዊና ለዴሞክራሲ መብቶች ትክክለ ምላሽ ለመስጠት ቃል የገቡትን የተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች ያቀፈ ጊዜያዊ የሽግግር መንግስት እንዲመሰረት እንጠይቃለን።

**በመጨረሻም**

***ለሁሉም ተቃዋሚ ድርጅቶችና በሃገሪቷ ለሚኖሩ ህዝቦች በሙሉ፣***

*የመለስ ዜናዊ ቡድን እንደ ኣመሉ የኦሮሞ ህዝብ ለመብቱ በሚታገልበት ወቅት የተቀሩት ህዝቦች የኦሮሞን ትግል በጥርጣሬ እንዲመለከቱና ትግሉ በነሱ ላይ ያነጣጠረ መስሎኣቸው ኦሮሞ ላይ እንዲነሳሱ ሲቀሰቅስ ቆይቷል።*

***በመሆኑም የሃገሪቷ ተቃዋሚ ድርጅቶች በሙሉ***

1. *የኦሮሞ ህዝብ ለትግል የተነሳበት ዋነ ው ምክንያት ስርኣቶች የሚያደርሱበትን የፖለቲካ ኣፈና ለማስቀረት እንጂ የህዝቦችን መብት ለመጋፋት ኣለመሆኑን፣ እንዲያውም የኦሮሞ ህዝብ ትግል ኣላማ ሁሉም ህዝቦች በገ ው መንግስት የሚደርስባቸውን ተመሳሳይ ኣፈና ለማስቆም በመሆኑ የሃገሪቷ ህዝቦች ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ከኦሮሞው ወገናቸው ጋር ኣብዮቱን እንዲያቀጣጥሉ ማስገንዘብና*
2. *የኦሮሞ ህዝብ ትግል መሳካት የተቀሩትንም የኢትዮጵያ ህዝቦች ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ህዝባቸውን በማስገንዘብ ይህንን ኣብዮት እንዲደግፉ ጥሪ እናስተላልፋለን።*

*ባጠቃላይ የችግሮቹ ሁሉ መንስኤ በህዝቦች ላይ የተዘረጋው የ"እኔ ኣውቅልሃለሁ" ፖለቲካ ስርኣት መሆኑን በማመን የዚህ ችግር ምንጭ የሆነውን የመለስ ዜናዊን ስርኣት ለማስወገድ የህዝብ ኣብዮት ማካሄድ ብቸ ው ኣማራጭ ሆኗል። ስለሆነም የኦሮሞ ህዝብና ሌሎችም የሃገሩቷ ህዝቦች ከጥር 22 ቀን 2012 ኣንስቶ በሃገሪቷ በሚጀመረው ኣብዮት እንዲሳተፉና ለዘመናት የተጫነባቸውን የጭቆና ቀንበር "በቃን" በማለት ኣሽቀንጥረው እንዲጥሉ ታሪካዊ ጥሪ ቀርቦላቸዋል።*

***የህዝቦች ኣብዮት ያሸንፋል!***

**ጥር 2012**

***የኦሮሞ ህዝብ ኣብዮት ኣስተባባሪ ጉባኤ (ኦህኣኣጉ) እና***

***ብሄራዊ የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ)***